# የወላጆች መመሪያ በኤኔት (ANet) አማካኝነት ስለሚሰጡ የዲስትሪክት ጊዜያዊ ፈተናዎች

DENVER PUBLIC SCHOOLS
Discover a World of Opportunity™

መመዘኛዎች ወይም ፈተናዎች ለተማሪዎች፣ ለወላጆች እና ለትምህርት ባለሙያዎች (አስተማሪዎች) ተማሪዎች የክፍል ደረጃቸውን እውቀት (ይዘት) ስለማወቅ አለማወቃቸው እና ለ21ኛው መ/ክ/ዘ ዝግጁ ሆነው ለመመረቅ ስለመቻል አለመቻላቸው ጠቃሚ መረጃ ይሰጣሉ። የእነዚህ ምዘናዎች ውጤት ልጅዎ በትምህርት ላይ ያለውን/ያላትን ለውጥ ከሚያሳዩ ማስረጃዎች መካከል አንዱ መለኪያ እንዲሆን የታሰበ ነው።

## ኤኔት ምንድን ነው?

ሁሉም ትምህርት ቤቶች ከ3ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎቻቸው በዓመት ሦስት ጊዜ የማንበብና የመጻፍ እና የሂሳብ ጊዜያዊ ምዘናዎችን እንዲሰጡ የዴንቨር የማህበረሰብ ትምህርት ቤቶች የሚጠበቀው ነው። ተማሪዎች የማንበብና የመጻፍ እና የሂሳብ መስፈርቶችን ለማሟላት የሚያደርጉትን መሻሻል በተመለከተ ለአስተማሪዎች መረጃ እንዲሰጡ በማሰብ የተዘጋጁ ከፍተኛ ጥራት ያላቸው፣ በጥንቃቄ የተዘጋጁ ጊዜያዊ ፈተናዎችን ለማቅረብ ኤኔት ከዲኤስፒ ጋር በጋራ ለመስራት መዘጋጀቱን ሲገልጽ በኩራት ነው። እነዚህ ምዘናዎች ተከታታይ እና ለማስተማር ስራ ተብለው የተዘጋጁ ናቸው። የእንግሊዝኛ ምዘናዎች በመረጃ መረብ አማካኝነት የሚሰጡ ሲሆን የስፓኒሽ ምዘናዎች ደግሞ በወረቀት ይሰጣሉ።

## ልጄ የሚፈተነው (የምትፈተነው) መቼ ነው?

በኤኔት የሚሰጡ ጊዜያዊ የማንበብና መጻፍ እና የሂሳብ ምዘናዎች በዓመት ሦስት ጊዜ ይሰጣሉ። ተማሪዎች ምዕራፎችን ሲያጠናቅቁ ተዛማጅ ምዘናዎችን ይወስዳሉ፣ እንዲሁም የመጨረሻ ማጠቃለያ ፈተና ለሁሉም ተማሪዎች ይሰጣል። የትምህርት ቤት አመራሮች በምዘና የጊዜ ማዕቀፉ ውስጥ ለተማሪዎቻቸው የተሻለ በሚመቸው ጊዜ ውስጥ መስጠት የሚችሉ ሲሆን ወላጆች የልጆቻቸውን ትክክለኛ የፈተና ጊዜ ከትምህርት ቤቱ ማግኘት ይችላሉ። አብዛኞቹ ተማሪዎች እነዚህን ምዘናዎች ከ60-90 ደቂቃዎች ውስጥ ያጠናቅቋቸዋል።

| | **ኤ1** | **ኤ1** | **ኤ2** | **ኤ2** | **ኤ3** | **ኤ3** |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | *የኢኤልኤ ምዘና የሚሰጠው በ፦ **ኦክቶበር 10** | *የሂሳብ ምዘና የሚሰጠው በ፦ **ኦክቶበር 20** | *የኢኤልኤ ምዘና የሚሰጠው በ፦ **ጃኗሪ 18** | *የሂሳብ ምዘና የሚሰጠው በ፦ **ጃኗሪ 17** | *የኢኤልኤ ምዘና የሚሰጠው በ፦ **ማርች 13** | *የሂሳብ ምዘና የሚሰጠው በ፦ **ማርች 16** |
| **የክፍል ደረጃ** | **የሙከራ ፈተና በ፦** | **የሙከራ ፈተና በ፦** | **የሙከራ ፈተና በ፦** | **የሙከራ ፈተና በ፦** | **የሙከራ ፈተና በ፦** | **የሙከራ ፈተና በ፦** |
| **3** | ኖቬምበር 4 | ኖቬምበር 2 | ፌብሯሪ 2 | ጃንዋሪ 31 | ሜይ 22 | ሜይ 22 |
| **4** | ኖቬምበር 4 | ኖቬምበር 2 | ፌብሯሪ 2 | ጃንዋሪ 31 | ሜይ 22 | ሜይ 22 |
| **5** | ኖቬምበር 4 | ኖቬምበር 2 | ፌብሯሪ 2 | ጃንዋሪ 31 | ሜይ 22 | ሜይ 22 |

| | **ኤ1** | **ኤ1** | **ኤ2** | **ኤ2** | **ኤ3** | **ኤ3** |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | *የኢኤልኤ ምዘና የሚሰጠው በ፦ **ኦክቶበር 10** | *የሂሳብ ምዘና የሚሰጠው በ፦ **ኦክቶበር 5** | *የኢኤልኤ ምዘና የሚሰጠው በ፦ **ጃኗሪ 18** | *የሂሳብ ምዘና የሚሰጠው በ፦ **ዲሴምበር 14** | *የኢኤልኤ ምዘና የሚሰጠው በ፦ **ማርች 13** | *የሂሳብ ምዘና የሚሰጠው በ፦ **ፌብሯሪ 22** |
| **የክፍል ደረጃ** | **የሙከራ ፈተና በ፦** | **የሙከራ ፈተና በ፦** | **የሙከራ ፈተና በ፦** | **የሙከራ ፈተና በ፦** | **የሙከራ ፈተና በ፦** | **የሙከራ ፈተና በ፦** |
| **6** | ኖቬምበር 4 | ኖቬምበር 18 | ፌብሯሪ 2 | ፌብሯሪ 3 | ሜይ 22 | ሜይ 22 |
| **7** | ኖቬምበር 4 | ኖቬምበር 10 | ፌብሯሪ 2 | ፌብሯሪ 17 | ሜይ 22 | ሜይ 22 |
| **8** | ኖቬምበር 4 | ኖቬምበር 9 | ፌብሯሪ 2 | ጃንዋሪ 15 | ሜይ 22 | ሜይ 22 |

## ልጄ የሚሰጠው(ጣት) ውጤት ምንድን ነው?

Interim Assessment results provide important measures in how well your student is progressing towards mastery of grade level standards so that youልጅዎ አሁን ባለበት (ባለችበት) የትምህርት ደረጃ ውጤታማ ሆኖ (ሆና) እንዲያጠናቅቅ (እንድታጠናቀቅ) እና ከዓመት ዓመት የትምህርት እድገቱ(ቷ) እያደገ እንዲሄድ በክፍል ደረጃው(ዋ) የሚጠበቀውን ምን ያህል እንዳሳካ(ች) የሚመዝን ጠቃሚ መረጃ ከጊዜያዊ ምዘናዎች ውጤት ይገኛል።

የኤኔት ምዘናዎች በመስፈርቶች ቅደም ተከተል የሚደረደሩ ውጤቶችን ስለሚሰጡ፣ ተማሪዎች በየትኞቹ መስፈርቶች ጥሩ እንደሰሩ እና በየትኞቹ ጽንሰ-ሃሳቦችና ክህሎቶች ደግሞ ተጨማሪ ልምምድ እንደሚያስፈልግ ለአስተማሪዎች፣ ለተማሪዎች እና ለቤተሰቦች የተሻለ ግንዛቤ ይፈጥራሉ።

## እነዚህ ውጤቶች ጥቅም ላይ የሚውሉት እንዴት ነው?

ጊዜያዊ ምዘናዎች አስተማሪዎች በተማሪዎች ትምህርት ላይ ያሉ ክፍተቶችን እንዲለዩና ተግባራዊ ርምጃ መውሰድ እንዲችሉ የሚረዱ መረጃዎችን ይሰጧቸዋል። አስተማሪዎች በማንበብና መጻፍ እና በሂሳብ የክፍል ውስጥ ትምህርት አሰጣጣቸውን ለመምራትና ለማሻሻል እና ተማሪዎች በትምህርት ደረጃው የሚጠበቁባቸውን መስፈርቶች ለመቻል በሚያደርጉት ጥረት ድጋፍ ለማድረግ የእነዚህን የምዘና ውጤቶች ሊጠቀሙ ይችላሉ።

## ተጨማሪ መረጃ

ምዘናዎችን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ የተጠያቂነት፣ ምርምር እና ግምገማ ድረ ገጽን ይጎብኙ፦ dpsare.com

በልጅዎ ትምህርት ዙሪያ ተሳታፊ እንዲሆኑ እናበረታታዎታለን። ልጅዎን በቤት ውስጥ ሊያግዙት(ዟት) የሚችሉበትን መንገድ በተመለከተ መረጃ ለማግኘት የልጅዎን አስተማሪ ለማነጋገር አያመንቱ።

በተጨማሪም፣ የሚከተሉትን እና ሌሎችንም ጠቃሚ መረጃዎች ለማግኘት ይህን ድረ ገጽ http://standards.dpsk12.org/standards-resources/ እንዲጎበኙ እንመክርዎታለን፦

- ለወላጆች የቴክኖሎጂ አጋዥ
- መረጃ ለእንግሊዝኛ ተማሪዎች
- የኮሎራዶ ግዛት መገልገያዎች

ምዘናዎችን በተመለከተ ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ካሉዎት፣ እባክዎ በቀጥታ የልጅዎን ትምህርት ቤት ያነጋግሩ ወይም ለቤተሰብ ምክር አገልግሎቶች በስልክ (720) 423-3054 ይደውሉ።